# ፌሽካና ፋሽኮ

(በማህሉ በቀለ - ቶሮንቶ)

ፌሽካና ፋሽኮ፣ ተገናኙና
ውሎ ሳያድር፣ ተጎዳኙና
ላይካካዱ፣ ተማማሉና
ጉዞ ጀመሩ፣ በትግል ጎዳና፡፡

ጨዋታን ‘ሚያመጣው፣ ጨዋታ ሆነና
አንዱ ስለሌላው፣ ማወቅ ፈለገና
ጥያቄና መልሱ፣ ተደረደረና
አንዴም ይወራና፣ አንዴም ይሳቅና
ውይይቱ ጦፈ፣ ሆነ አሸወይና፡፡

ያልተወራ የለም፣ ያልተደሰኮረ
ምድረ ፖለቲካ፣ እየተዘረዘረ
ስለሰላም ትግል፣ ስለዲሞክራሲ
ሰለአገር ግንባታ፣ ስለቢሮክራሲ
ሰለፍርድ ስለህግ፣ ስለሰው ልጆች መብት
ስለልዑላዊነት፣ ስለህዝብ አንድነት
አጀንዳው ታሰሰ፣ በአይነት በአይነት፡፡

ስማ አለ ፌሽካ፣ ለፋሽኮ ጓደኛው
እንዳያስቀይመው፣ ፍርሀት እየገባው
ማዳመጥ መስማትን፣ ስለማያውቅ ከቶ
ደፈርፈር አለና፣ ግራ ቀኙን አይቶ
እንዲህ ሲል ጀመረ፣ ፌሽካችን በርትቶ፡፡

ይመስለኝ ነበረ፣ ብዙ ነገር ‘ምታውቅ
ክህደትን አውግዘህ፣ የምትቆም ለሐቅ
ይመስለኝ ነበረ፣ ተግባር ያዳበረህ
ይመስለኝ ነበረ፣ ዕውቀት ያጠለቀህ
ይመስለኝ ነበረ፣ ማስተዋል የሰጠህ
ይመስለኝ ነበረ፣ ኑሯችን የገባህ
ምኑንም አታውቅም፣ ቢከፍቱህ ተልባ ነህ
ለካስ ባዶ ጣሳ፣ ደንበኛው ፋሽኮ ነህ፡፡

ፎርምና ቁመናህ፣ ሁናቴህ ስቧቸው
ድንቡሽቡሽ ፍርጥምጥም፣ ብለህ ታይተሀቸው
ይዘትና ቅርፅህ፣ አልለይ ብሏቸው
ስንቶቹ ተጠጉህ፣ ሙሉ መስለሀቸው
ጎዶሎ መሆንህ፣ መቸ ታወቃቸው፡፡

ፋሽኮም መደፈሩ፤ ንድድ አድርጎት
እንዲህ አይነት ዘለፋ፤ አናቱን መቶት
ይጉረጠረጥ ጀመር፤ ሁኔታው ገርሞት፡፡

ትንሽ ቆየት ብሎ፤ አሰብ አረገና
እንዲህ ይለው ጀመር፤ ፊሽካን በጥሞና

ስማ አንተ ፊሽካ
ቃልህ አያረካ
ስራህ አያስመካ
ተደመጥኩኝ ብለህ፤ ነገር ስታቦካ
ስትዋሽ ስትቀጥፍ፤ ስተርክ ትረካ
አፍህን ስትከፍት፤ ወሬ ስታበዛ
ምነው አልነገሩህ፤ እነደሆነክ ሞዛዛ
ዝም ብሎ የሰማህ፤ እንዳይመስልህ ዋዛ፡፡

እኔ ፋሽኮ ባዶ፤ ከሆንኩኝ ባንተ ቤት
አንተም ፊሽካው ያው ነህ፤ ልንገርህ በኔ ቤት፡፡

አንተም ስለምትጮህ፤ ትንሹ ጡሩምባ
እኔም ባዶ ቀፎ፤ ስለሆንኩኝ አልባ
ሌላ ሰው እንፈልግ፤ ከኛ የተሻለ
በዕውቀት በሃሳብ፤ በደንብ የበሰለ
በተልካሻ ባህርይ፤ አጉል ያልቀለለ
ለህሊና እንጂ፤ ለሆድ ያላደረ
ለእውነት ተሟጋች፤ ህዝቡን ያከበረ፡፡

ፊሽካ ድምፅ ማውጣትህ፤ በሀይል ሲነፉህ ነው
የኔም ባዶ መሆን፤ ‘ሚሞላኝ ጠፍቶ ነው
ሰለዚህ ፊር በል፤ የሰው ያለህ ብለህ
ደጋግመህ ተጣራ፤ ድረሱልኝ ብለህ
እኔም ሆዴን ሰፋ፤ አድርጌ ‘ቆያለሁ
ሞልቶ እስከሚፈስ፤ ትግስት አደርጋለሁ
አንተም ከተጣራህ፤ እኔም እችላለሁ
ይኸው ነው መንገዱ፤ ሌላ ምን እላለሁ፡፡